# ኢትዮጵያችን

*አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 2 ቁጥር 3 ታህሳስ ፲ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ.ም.

## ሁሉም ዘር ለኢትዮጵያ

(ድምጽ ቅጅውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ https://www.youtube.com/watch?v=sGuG88i1xes)

አምባገነን ገዥዎች እጃቸውን ተይዘው እስኪዋረዱ ድረስ የመጨረሻ ሰዓታቸው አይታያቸውም። የሕዝብ ኃይል ምን ቢበረታ በያዙት መሳሪያና በሚመሩት የሥለላ ድርጅት በመተማመን ያች የመጨረሻ የጣር ቀን እስክትመጣ ይፈራገጣሉ። ሁለት እጃቸው ሕዝባዊ ካቴና እስኪገባለት ድረስ ሕዝብን ይንቃሉና። ሁልጊዜ እነሱ ያቀዱት የተንኮል መረብ ብቻ አጥማጅ ይመስላቸዋል። እንዴት አድርገው ሕዝባዊ ቁጣን ለማፈን ሲጥሩ እንጂ "አሁንስ ይበቃናል" ብለው የሕዝብን ሃያልነት ሲቀበሉ በታሪክ አልታዩም። የመጨረሻ እጣ ፈንታቸው ቢታያቸውም በሥልጣን ዘመናቸው የዘረፉት የሀገርና ሕዝብ ንብረትና ሀብት፣ ያለ አግባብ ያፈሰሱት የንፁሃን ደም፣ ሥልጣናቸውን መከታ አድርገው ያፈናቀሉት ኅብረተሰብ ብሶትና ሰቆቃ፣ ሌላም ሌላ ሲታያቸው የመጨረሻውን የጥፋት መንገድ ይመርጣሉ። ያልተረዱት ግና የመጨረሻው ሰዓት ጥይት ቢተኩሱት አይመታም፣ ሬድዮናቸው ቢያቅራራ አይሰማም፣ ከግራ ሲሉት ከቀኝ፣ ከፊት ሲሉት ከኋላ ሚከባቸውን ሕዝባዊ ማዕበል አይረዱትም፣ ይንቁታልና አወዳደቃቸው ከንቱ ይሆናል። እንደ ዘመናቸው ፍጻሜያቸውም የከንቱ ከንቱ ይሆናል።

የወያኔ/ህወሀት አገዛዝ በሥልጣን በቆየበት 26 ዓመታት ለሕዝብና ለሀገር እንዲገዛ፣ ከሕግ በታች እንዲሆን ያልተደረገ ጥረትና ሙከራ አልነበረም። ሥልጣን ከመያዙ በፊትም ሆነ በኋላ ሕዝባዊ መሠረት የሌለው ይህ አገዛዝ እራሱን ለመለወጥና የሀገርና የሕዝብ ስሜትን ለማዳመጥ የነበረውን በርካታ ዓመታት በእብሪትና በንቀት የበላ አገዛዝ ነው። ትዕግስትና እሺ ባይነት ያልተለየው የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን የግፍ አገዛዝና መከራ ከዛሬ ነገ ይሻል ይሆናል በሚል ሩብ ምዕተ ዓመት ተሸክሞታል። የሕዝብ ልጆች ቆሎ፣ ድንች፣ ሎተሪ ወዘተ እየሸጡ አገዛዙን ተሸክመውታል። ሴቶች እህቶቻችን በየመንገዱና ቡና ቤቱ ክብራቸውን ለማዋረድ እየተገደዱ፣ ሊስትሮው፣ የእኔ ብጤው "የነገን ማን ያውቃል" እያለ ዓመታትን ቆጥረዋል። ወጣቶች ተስፋቸው ወያላነትና ቦዘኔነት መሆኑን "አሜን" ብለው አስተናግደዋል። የቀን ሠራተኞች ትርፍራፊ ጉርሻ ተሻሚ ሁነው ኑረዋል። የመንግሥት ሠራተኞች በቀን አንዴ ጎርሰው "ተመስገን" ብለዋል። ቤተሰቦች ያገኟትን ተሻምተውና ረሃብን ጥጋብ አርገው አንጀታቸውን አስረዋል። አዛውንት እናትና አባቶች "ምነው አምላኬ እድሜዬን አረዘምከው? ምን ጉድ እያሳየህ ትቀጣኛለህ?" እያሉ ተክዘዋል። ሀገር ከእንዲህ ዓይነቱ በረሀብ ከተቀጣ ኅብረተሰብ መተካት የሚገባትን የነገ ተስፋዎቿን አጥታለች። "ትውልድ ይመጣል ትውልድ ይሄዳል" እኛ ዘንድ ሲደርስ ተቀጭቷል። የአደንዛዥ ዕጽ ተገዥ ወጣቶችን ቤቱ ይቁጠራቸው። ሕፃናት በያዙት ጨርቅ ከመኪና ጭስ ነዳጅ ለመሳብ የሚያደርጉትን ሽሚያ ለተመለከተ፣ በሲጃራና ጫት የተከበቡትን ሕጻናት ላየ "እውን ኢትዮጵያ በደኋ ምን ያህል ቢከፋ ነው ለዚህ የዳረጋት?" ያሰኛል።

በሚገባ ላየውና ለመረመረው ግና ይህ እርግማን ሳይሆን የሰው ልጅ፣ ያሳደገችው ልጇ እሳት ሆኖ እየለበለባት፣ እያቃጠላት ነው። የዛሬ ወጣት ትውልድ ወያኔ/ህወሀት ሥልጣን እንደያዘ ኢትዮጵያ አኩሪ ትውልድ እንዳይኖራት ከልጅነት ጀምሮ በተለያየ አቅጣጫ በአጉል ባህል ሊበርዛቸውና ሊያሸመደመዳቸው የሞከራቸው ናቸው። ኢትዮጵያ ተተኪ ትውልድ እንዳይኖራት ከጅምሩ ሕፃናት ሊመለከቱት የማይገባን የውጭ ፊልም በየጉራንጉሩ እንዲታይ በማድረግና ተያይዞ የተሰበሰቡትን ሕፃናት በሲጃራ፣ ሀሺሽ፣ ጫት፣ ሺሻ ሱስ በማጥመድ የሀገር ሸክም ሁነው ይቀሩ ዘንድ የዛሬ 26 ዓመት የታቀደው ሤራ ዛሬ ሺዎችን አፍርቶ ከዚህ አድራጎት መራቅ እንደ "ፋራና ከርፋፋ" አስቆጠረበት ዘመን ደርሰናል። ዛሬ በሀገራችን ያለ ዕድሜ ወሲብ ማካሄድ የተለመደ ነው። ከስም አወጣጥ ጀምሮ፣ በአለባበስ፣ በአበላል፣ በአካሄድ፣ በቋንቋ የባዕድ አምላኪ ዜጋ ሲበራከት ማየቱ ወያኔ ትላንት የዘራው መርዘኛ ዘር ማበቡን መስካሪ ነው። በሃይማኖቱ ብንሄድ ፈርሃ እግዚአብሔር ተረስቶ ታቦት ሚሰረቅበት ዘመን ተደርሷል፣ ለእምነቱ ያልተገዛ ቄስና ጳጳስ ያገኘች ቤተ ክርስቲያን በወያኔ አይተናል።

ከወያኔ የዘርና የቋንቋ ከፋፍለህ ግዛ ባሻገር ኢትዮጵያን ባህሏንና ሃይማኖቷን በማዳከም በዘላቂነት እንዴት ልትሸመደመድ እንደምትችል ዘላቂ ግቡ አድርጎ የተነሳ ወያኔ መውደቂያው ቢዳረስም ሸክማችን ግና ቀላል አይደለም። እንደ ዘራችን ያለንን አኩሪ ባህል ወያኔ ሸርሽሮታል። ድሮ ከገበያ ዕቃ ይዘው የሚመጡ እናትን ለመቀበል ያለው እሽቅድምድም ዛሬ ይዘው የሚመጡት ከተገኘም አንቱታና አክብሮት በሌለው መንገድ "ስንት ትከፊያለሽ?" ሆኗል። ቤት ጠፍቷቸው የጠየቁ አዛውንት ኪሳቸውን መተማመን አለባቸው። ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቤት የቀየረ ዕቃው ቢሸጥ የማያወጣውን ለማውረጃና ለመጫኛ ይጠየቃል። ታክሲ ተሳፍራ "መልሴን" ያለች ወጣት እርግጫው ቢቀርላት ግልምጫና አስነዋሪ ስድብ ትሸለማለች። ይህ ሁሉ የደረስንበት አሳፋሪ ዘመን ትውልዱን ለመውቀስ ሳይሆን በእንዲህ ያለ የረቀቀ ዘዴ ወያኔ የኢትዮጵያን ልጆችና ወጣቶቿን ለማሽመድመድ እንደሞከረ ለማሳየት ነው። አንድ ሀገር ተተኪ ዜጋዋ ከተሸመደመደ ምታመራው ወደ ውድቀት መሆኑ አያጠራጥርም። ለወያኔ ኢትዮጵያ ማለት በመጠኑም ቢሆን ትግራይ ክልል ብቻ ነውና ሌላው ክፍል እንደ አይጥ የሚቦረቡሩት ጎተራቸው ነው። ለዚህም ነው የ26 ዓመት የወያኔ/ህወሀት ዕድገት ያስመዘገበው ቢኖር አሁንም ከሻማ ብርሃን አለመውጣትን፣ ጀሪካን ይዞ ውሃ ለማግኘት ቀን ሙሉ መሰለፍን ነው። ሌላው ክልልና ዘር ትውልድ እንዳይበቅልበት በተለያየ መንገድ ሲሸመደመድ ጎልቶ የሚወጣውና ወደፊት "ተፈላጊ ዜጋ" የትግራይ ልጅ ብቻ ነው የሚል ቅዠት አለባቸውና። ሙሉ በሙሉ መደምደም አግባብነት ባይኖረውም ዛሬ "ተማረ፣ ሥራ ያዘ፣ ሥልጣን አገኘ፣ ወደ ውጭ ተላከ፣ ነጋዴ ሆነ፣ እሱ እኮ" የተባለለት በአብላጫው ለትግሬው ኅብረተሰብ እንዳደላ መስካሪ አያሻም። ይነገር ከተባለ ኢትዮጵያ ውስጥ የብሔር ጭቆና ያለው ዛሬ ነው።

ወያኔና ሻቢያ ሀገሪቷን ሲቆጣጠሩ "የመቶ ዓመት የቤት ሥራ እንሰጣቸዋለን" ያሉትን ዛሬ ላይ ሆነን ስንመለከተው እውነትም ተሰጥቶናል ያሰኛል። ወያኔ በዘርና በሃይማኖት የኢትዮጵያን ልጆች ለማባላት ያለው ዕቅድ በምንም መንገድ ከአጀንዳው አይወጣም። ዛሬ ወያኔ/ህወሀት አንድ እቅዱ እያበቃለት ይገኛል። እራሱ ክልል ብሎ በቋንቋ በከፋፈለው የትኛውም አካባቢ መንግሥታዊ አስተዳደሩ እያበቃለት ይታያል። በተለያዩ አካባቢ ባሉ ተቃውሞዎች ሳቢያ ትምህርት ቤቶች፣ የንግድ ተቋማት እንቅስቃሴሃቸው እየተዳከመ መጥቷል። በዘረኝነት የገዛው ወያኔ/ህወሀት የዘር ዓመጽ እያናጋው ነው። የኦሮሞ ልጆች እምቢተኝነትን ሊገታው ተስኖታል፣ የአማራን ለእልውናው የሚያደርገው ተጋድሎ እየለበለበው ነው። በሱማሌ፣ በደቡብ፣ በጋምቤላ በሁሉም የሀገሪቷ ክልሎች ጩኸቶች የወያኔን ማብቃት እያስተጋቡ ናቸው።

*ወያኔ አንድ የመጨረሻ ሂደቱን ሲሞክር በየአካባቢው ያሉ እንቅስቃሴዎች ደግሞ ሀገራዊ መልክ ይዘው በተቀናጀ መልኩ ኢትዮጵያን ያድናሉ ወይስ ሁሉም የዘሬን ብሎ በየፊናው ይጓዛል? አሳሳቢና ሊታይ የሚገባው ወቅታዊ ጉዳይ ነው። <u>አራት ነጥብ አድርገን ልናሰምርበት የሚገባ ጉዳይ በምንም መልኩ ትላንትም፣ ዛሬም ሆነ ነገ ወያኔ/ህወሀት ለኢትዮጵያ ስለ ኢትዮጵያ እንደማያስብ ነው።</u> ኢትዮጵያ በወያኔ ያላት ዕድል መድቀቅ ነውና መወገድና ቃሉ ካልከበደን መውደም ያለበት አገዛዝና ድርጅት ወያኔ/ህወሀት ነው። የ26 ዓመት የሀገርና ሕዝብ ብሶትና እየዬ የወለደው እምቢተኝነትና ሕዝባዊ ቁጣ እየጋለ ሲመጣ "የወያኔ ለቅሶ መልሶ መላልሶ" እንዲሉ "ተሃድሶ፣ ሹም ሽር" ቢሉት ሰልችቷልና አድማጭ አያገኝም። በየጊዜው በአካሄደው ተቃውሞ እየተሸነገለ ልጆቹን ለእሥርና ሞት የገበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዳግም እንደማይታለል እያሳየ ይገኛል።*

*በሌላ በኩል "ሀገራችንን ሳናይ እርጅናው ይዞን ሊሄድ ነው" ብለን ወያኔን ለመለማመጥ ካልፈለግን በቀር ይህ አገዛዝ እንደ ደርግ ኢሠፓ ማብቃት ያለበት ነው። በአገዛዙ የተኮለኮሉና ተጠያቂዎች የሕግ መዝገብ የሚከፈትላቸው መሆኑን አበክረን ስንናገር የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃ እናወጣለን። በሌላ በኩል "ዘር ከልጓሙ ይስባል" እንዲሉ ምንም ቢሆን የኛው ናቸው ከሚል በዘረኝነት ወጥመድ የተጠመዱ የዘር ፖለቲካ ድርጅቶች ወያኔ/ህወሀት ሊታደስ እንደሚችልና ስለ ሰላማዊና ብሔራዊ ዕርቅ አድምጠን ቢሉ ባያስገርምም ተደጋጋሚ ዕድሉን ለቀበረ ወያኔ የመጨረሻ ዕድሉ ግባተ መሬት ሲሆን የኢትዮጵያና የሕዝቧ አንድነት ይጠናከራል እንላለን። ሰላምና ብሔራዊ ዕርቅ የወያኔ/ህወሀት ሥርዓት እንዲያበቃ ታጋይ የፖለቲካና ማህበረሰብ ድርጅቶች ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችን አካተው ለነገዋ ኢትዮጵያ የሚመክሩበት ጉዳይ መሆን ይገባዋል ስንል "**አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ**" አቋማችንን እናስቀምጣለን። ሰላምና ብሔራዊ ዕርቅ በአለፉት አርባ ዓመታት ሀገርን የበደሉና በትውልድ ደም ተጠያቂዎችን "ይቅር ለእግዚአብሔር" ከማለት ውጪ ዳግም ለስልጣን ለማብቃትና የግፍ ዳውላቸውን ሕዝብ ላይ ለመጫን መሆን የለበትም።*

*አምባገነንና ገዳይ ሥርዓት ዳግም በሀገራችን እንዳይከሰት ካስፈለገ በሀገር ሀብት ዘረፋና የሕዝብ ሕይወትን የቀጠፉ ሕግ መኖሩን እንዲያውቁ ይገባል። የወያኔ/ህወሀትን 26 ዓመት ግፍና በደል ዘንግቶ ይህንን አገዛዝ የቀጣይ መንግሥት ተጋሪ ማድረግ ለኢትዮጵያም ለሕዝባችንም እንደማይበጅ ለመግለጽ እንወዳለን። እርግጡን ለመናገር ገና ከጅምሩ የፈሰሰው የበደኖና የአርባ ጉጉ ደም ወያኔ/ህወሀት ላይ ይጮሃል። ሕፃን ሽብሬ ደሳለኝን ጨምሮ የ1997ቱ በትንሹ የ196 ንፁሃን ሕይወት "የፍትህ ያለ" ሲል ወያኔ/ህወሀት ላይ ያንባጥራል። የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የጋምቤላዎች፣ በአሸባሪ ስም በጅምላ የተጨፈጨፉ የኦጋዴንና የሱማሌ ኢትዮጵያውያን ሕፃናት፣ አዛውንትና ወጣቶች ሕይወት ለሕግ ካልቀረበ ሕግ ምኑን ሕግ ሆነ? ጊዜ አግኝቶ ያለአግባብና ያለፍርድ የሕዝብ ልጆችን የፈጀ ወንጀለኛ ጊዜ በሕግ እንደሚዳኝው ካልታየ ለኢትዮጵያ ዕምባ ምኑን ደረስንላት? የእናቶች እየዬ፣ ያባቶች ትካዜ፣ የሕፃናት ዋይታ፣ የወጣቶች ሰቆቃ ዳግም በሀገራችን እንዳይከሰት "የሕግ ያለህ!" ካልተባለለት እንዴት ዋስትና ይገኛል።*

*"ጅብ እማያውቁት ሀገር..." እንዲሉ ዛሬ የደርግ ገዳዮችና ባለሥልጣናት በየፖለቲካ ድርጅቱ ውስጥ ተሰግስገው ስለ ሰላምና ብሔራዊ ዕርቅ ከወያኔ/ህወሀት ጋር ቢሰብኩ "እባብ ለእባብ" እንላቸዋለን። ወያኔ/ህወሀት መውደም ያለበት አገዛዝ ስንል ዘራችን ተነካ የሚሉ ተቃዋሚዎች ካሉ "የትግራይ ሕዝብ ለኢትዮጵያ አንድነት" እንላቸዋለን። ደግመን ደጋግመን እንዳስነበብነው አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ስንል ትግራይን ይዘን፣ ኦሮሞን ዋልታ አድርገን፣ አማራን አቅፈን፣ ሁሉንም አናሳ ጎሳዎች አለንላችሁ ብለን፣ ዘራቸውና ማንነታቸው በኢትዮጵያዊነት ብቻ ያሉ ወገኖችን አካተን እንደሆነ ግልጽ ማድረግ እንወዳለን። ከእንግዲህ <u>"ሁሉም ዘር ለኢትዮጵያ!"</u> የወቅቱ መፈክር መሆን ይገባዋል።*

የኢትዮጵያን አንድነት ባስጠበቀ መልኩ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት ካስፈለገ ዘረኝነት ከወያኔ/ህወሀት ጋር ማብቃት ይኖርበታል። በሀገራችን ኢትዮጵያ ከሰማንያ በላይ ቋንቋዎች አሉና በዘርና ቋንቋ መሸንሸን ከመጣ ማንም ማንንም ሊውጥ እንደማይችል ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባዋል። ***ኢትዮጵያ ሀገራችን አንድነቷን ጠብቃ ሁሉም ነገድ/ጎሳ ያልተገደበ የዜግነት መብቱን ተጎናጽፎ ወደ ልማትና ዕድገት ጎዳና ሀገራችን እንድታመራ "ሀ" ብለን እንጀምር ከተባለ ከወያኔ/ህወሀት የምንወስደው ቢኖር የተጨማለቀ ሥርዓቱን ቀብረን ሀገራችንን ብቻ ነው።***

***ውድ የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ!***

በየአካባቢው ለሚደረገው ሕዝባዊ መነሳሳት "*አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ*" ያልተቋረጠ ድጋፋችንና እገዛችን ከጎናችሁ አለ። ሰሞኑን በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች እየተካሄደ ያለው ዘርን ያነጣጠረ መደባደብና፣ መገዳደል ወያኔ የሚፈልገው ሂደት ነውና አቅጣጫውን እንዳይስት ልናስገነዝብ እንወዳለን። ወያኔ/ህወሀት ዛሬ የመጨረሻው ሰዓት ላይ ነውና የተጀመረውን ትግል በማኮላሸት ዕድሜ ለመግዛት የማይፈነቀለው ተንኮል የለምና ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባዋል። ወያኔ/ህወሀት አማራና ኦሮሞ እንዲተላለቅለት፣ ክርስቲያንና እስላሙ ኅብረተሰብ እንዲፋጅለት ትልቅ ምኞት አለው። ሀገሪቷን ሊያወድም የመጣ አገዛዝ ነውና ኢትዮጵያን በታትኖ መንግሥት አልባ ለማድረግ ፍላጎቱ በመሆኑ ነው "እኛ ከሌለን ኢትዮጵያ አበቃላት" ፉከራው። ይህ እንዳይሆን ወያኔ/ህወሀትን እየተፋለማችሁ ያላችሁ በተለይ የአማራና የኦሮሞ ልጆች እንኳንስ እርስ በርሳችሁ የትግራይ ወገኖቻችሁን እንዳታጠቁ ልናሳስብ እንወዳለን። ወያኔ/ህወሀት የትግራይን ጎሳ መጠቀሚያ አደረገው እንጂ አልጠቀማቸውም። አንድ ኢትዮጵያ ስንል የትግራይ ተወላጆችን ይዘን ነውና የተጀመረው ትግል በወያኔ ወጥመድ እንዳይሰናከል መጠንቀቅ ያስፈልጋል። የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ እናስወግድ ስንል የትግራይ ጎሳን ጭምር ነፃ እናውጣ ማለታችን ነውና።

ለትግራይ ተወላጆችና ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ልንል የምንፈልገው ቢኖር ትግራይ ለኢትዮጵያ መሠረቷ ናትና ሀገራችንን እናድን። የትግራይን ህብረተሰብ በወያኔ/ህወሀት ላይ በተጠናከረ መልኩ ለማነሳሳት ትኩረታችን ይሁን። ዛሬ የወያኔ የዘር ፖለቲካ በዘር መነሳሳትን ግድ ቢልም "የትግራይ ዘር ለኢትዮጵያ" ብላችሁ ተነሱ። አማራውና ኦሮሞው እንዲሁም ሌላው የኅብረተሰብ ክፍል በየአቅጣጫው በወያኔ/ህወሀት ሥርዓት ላይ ሲያምጽ የናንተ ዝምታ የወያኔ ደጋፊ ያስመስላችኋልና የታሰራችሁበትን ወጥመድ በጥሳችሁ መውጣት ይኖርባችኋል። የትግሉ ተሳታፊ በመሆን እኛም ለኢትዮጵያ ብላችሁ ከኦሮሞና አማራ እንዲሁም ሌሎች ጎሳዎች ጎን ሠልፋችሁን አሳምሩ። የዚህ ጊዜ ወያኔ/ህወሀት አገዛዝና የትግራይ ህብረተሰብ የተለያዩ መሆናቸውን ታስመሰክራላችሁና። የዚህ ጊዜ በረሃብ ከተቀጣው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይልቅ በጥጋብ ላበጠው ወያኔ/ህወሀት ወየውለት። የመጨረሻው ሰዓት ለወያኔ "አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ" ሲተገበር የኢትዮጵያ ትንሳዔዋ ይሆናል። ኢትዮጵያን ያልን ኢትዮጵያዊነትን በኦሮምኛ፣ ኢትዮጵያዊነትን በትግርኛ፣ ኢትዮጵያዊነትን በአማርኛ፣ ኢትዮጵያዊነትን በጉራግኛ፣ ኢትዮጵያዊነትን በአፋርኛ፣ ኢትዮጵያዊነትን በወላይታ፣. . . ኢትዮጵያዊነትን በኢትዮጵያ ካታገልን ድሉ የሀገራችንና የሁላችንም ይሆናል። ይህን ጊዜ በኢትዮጵያዊነት ዘራችን ይበዛል፣ ባህላችን ይዳብራል፣ ቋንቋችን ይፈለጋል፣ ሃይማኖታችን ይጸናል፣ ሕዝባችን ሀሴት ያደርጋሉ። ኢትዮጵያ ኢትዮጵያችን ትሆናለች!!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!
እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!!!
"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"
ታህሳስ 6 ቀን 2010 ዓ.ም. (December 16, 2017)

**<u>ማሳሰቢያ ፡</u>**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachen